# <u>ደራሲው</u>



ትንሽ ተቆጥቼ፣ ብዕርሬን ኣንስቼ
ጫፉን ኣሿሿልሁተ፣ ስለቱን ኣየሁት
እንደ ጦር ተመዝዞ፣ በጣቶች ተይዞ፣
የደራሲ ምርኩዝ፣ የዕድሜ ልክ ጉዞ፣
ቀለም ኣልነበረኝ፣ ፈለግሁኝ፣ ፈለግሁኝ!
ከጭንቅላቴ ውስጥ፣ ከኣንጎሌ ጠቀስሁኝ...
ረቂቅ ፍልስፍና፣ ጥልቅ ምርምር፣
ወረቀት ኣልቀረኝ እንደ ሳር ክምር
ጻፍሁኝ! ጻፍሁኝ! ጻፍሁኝ! ምንም ሳላስቀር!

ኣንጎል ነጫጭባ፣ ኣይደምቅም ቀለሙ፣
ኣንብቦ የገባው የለም በዓለሙ...



ከዚያም ሌላ ዘዴ እያሰብኩ ሳሰላ፣
ተመራመርኩና ኣገኘሁኝ መላ፣
ጫካ ተደብቄ በቅጠል ከለላ፣
በውድቅት ሌሊት ማንም ሰው ሳያይ፣
ብዕሬን ኣቅንቼ በደረቴ ላይ
ልቤንን ወጋሁት፣ ደሜን ኣጠጣሁት፣
ብዕሬም ደም ጠብቶ ወጣ እንደ ግስላ
ከዚያም ስለ ስሜት፣ ጻፈ ሰለ ፍቅር
መንፈሳዊውና ስለ ስጋ ግብር

ጻፈ! ጻፈ! ጻፈ! ኣንድም ሳያስቀር...
ሰው ግን ደሙን ፈርቶ ይጠየፍ ነበር።



ይህ ዘዴም ኣልሠራም፣ ታድያ ምን ይሻላል?
ስለ ሰዎች ችግር መጻፉ ይቀልላ?
ብየ ሳሰላስል፣ ሳወጣ፣ ሳወርድ
መታኝ ብዙ ፀሓይ፣ መታኝ ብዙ ብርድ፣
ዳግም ደረቴ ላይ ብዕሬን ወግቼ
ከሓሞት ከረጢት ቀለም ኣጠጥቼ
እንዲያው የሰው ልጆች ኑሯቸው መራራ
ብዙ ፍዳ ሲያዩ ለቁራሽ እንጀራ
እያልኩ የዓለም ስቃይ ስቆጥር፣ መከራ...

እውነት ኣልፈለጉም ስዎች ግን ፍጹም
የሚሰማኝ ጠፋ፣ ኣንድ እንኳን የለም!

ከዚያም ያ ደራሲ ልምከርህ ኣለና
ሰገራ ቤት ሄዶ እዳሪ ወጣና
ብዕሩን ጠቀስ ኣድርጎ ቢለቀልቀው
ሰው ሁሉ ወደደው፣ ሁሉ ኣደነቀው

ዓለሙን በሞላ ኣነቃነቀው...
ከዚያም ስማ ብሎ ምስጢር ሲያስረዳኝ
“ጥልቅ ኣትመራመር፣ ውስጥ ኣትግባ!” ኣለኝ
“የኑሮን መከራ፣ ጥላቻ፣ ፍቅር
ሓቁን ኣታፍረጥርጥ፣ በረቂቅ ምስጢር”

“የኣንገት ላይ-ላዩን ይወደዋል ሰው
ቡልሺት! ብልሽት! ኣድርገህ እንዲሁ ተወው።”

**ገ/ኢ. ጐርፉ።**

